# ወርሃዊ የአየር ጠባይ

# ግምገማና እና ትንበያ መጽሔት

## ከሴፕቴምበር 1-30/2023 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ እንዲሁም

## ከኦክቶበር 1-31/2023 የሚኖረው የአየር ጠባይ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ኦክቶበር 2023
አዲስ አበባ

ርዕስ　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　ገፅ


እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2023 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ ....... 1

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2023 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ....... 3

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2023 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት ....... 4

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2023 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ....... 5

እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2023 የነበረው የአየር ጠባይ በእርሻ ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ....... 6

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ....... 6

እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2023 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ....... 7

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ....... 7

እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2023 የሚኖረው የአየር ....... 8

ጠባይ አዝማሚያ ....... 8

ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከኦክቶበር 1-31/2023 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ....... 9

እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2023 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ....... 9

እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2023 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በውሀው ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ....... 10

# እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2023 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ

በመደበኛ ሁኔታ በሴፕቴምበር ወር የክረምቱ ዝናብ በምስራቅ፣መካከለኛ እና ሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ቀስ በቀስ በመጠንም ሆነ በስርጭት እየተዳከመ የሚሄድ ወር ነዉ፡፡ ባለፈው ሴፕቴምበር ወር የመጀመሪያው አስር ቀናት የዝናቡ ስርጭት በምዕራብ፣በደቡብ ምዕራብ እና መካከለኛዉ እንዲሁም በሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተሻለ የዝናብ ስርጭት ነበራቸው፡፡ በሴፕቴምበር የሁለተኛዉ አስር ቀናትም በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ የዝናቡ ስርጭት እና መጠን በተመሳሳይ ሁኔታ ተጠናክሮ የቀጠለበት ነበር፡፡ በሶስተኛው አስር ቀናት ደግሞ የዝናቡ ስርጭት ከቦታ ሽፋን አንጻር ሲገመገም በሀገሪቱ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ የሆኑ አከባቢዎች ላይ ከአንደኛዉ እና ሁለተኛዉ አስር ቀናት የተሻለ እና የተስፋፋ የዝናብ ስርጭት ነበራቸው፡፡ በሴፕቴምበር ወር ዉስጥ ከባድ ዝናብ ከተመዘገበባቸው ስፍራዎች መካከል በጎንደር 33.4፣በጎሬ 38.1፣ በጅማ 33.5፣36.5፣37.7 በነቀምቴ 30.7፣38.4፣45.5፣59.6፣በአማን 33.2፣በአቦቦ 30.4፣ በአሊያ 46.7፣በሆሮማያ 30.0፣ በአልጌ 30.0፣38.0፣60.0፣68.0፣ በአንገርጉትን 33.4፣53.6፣በበደሌ 35.8፣በብላቴ 43.5፣ በአርጆ 34.4፣34.5፣ በቡሬ 45.2፣34.5፣በቡኢ 52.9፣በጭራ 36.6፣ በቻግኒ 30.6፣ በዳንግላ 31.0፣ በደብረ ታቦር 35.3፣ በዶሎመና 40.0፣ በፉኚዶ 51.8፣34.8፣በጋምቤላ 34.3፣ በጋቲራ 37.8፣35.8፣40.8፣በገለምሶ 37.2፣በጎሬ 64.7፣በወሊሶ 38.6፣ በጊዳአያና 35.1፣35.5፣66.1፣74.0፣ በጊምቢ 51.5፣በጉንዶመስቀል 32.0፣ በእንድብር 42.1፣በጃራ 30.0፣በጂንካ 48.2፣ በካቺሴ 40.1፣ በማሻ 80.4፣80.6፣ በአዳማ 39.0፣በነጆ 54.3፣40.2፣በቴፒ 33.8፣በፓዌ 40.2፣በሻዉራ 52.4፣108.4፣በሻምቡ 40.0፣44.7፣በስሪንቃ 83.5፣በላሬ 82.2፣በሊሙገነት 44.5፣30.5 እንዲሁም በሰኮሩ 43.0 በሚ.ሜ ይገኙበታል፡፡


ባለፈው የሴፕቴምበር ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ሆሮ ጉዱሩ፣ ቄለም ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ምስራቅ እና ደቡብ ምዕራብ ሸዋ፣አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ምዕራብ እና ደቡብ ምዕራብ ሸዋ፣ምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፣ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ፣ቦረና፤ከሱማሌ ክልል ሲቲ፣ፋፋን፣አፍዴር፣ሊበን እና ዳዋ ዞኖች፤ከአማራ ክልል ሰሜን፣ማዕከላዊ እና ደቡብ ጎንደር፣ዋህግምራ፣ሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣የኦሮምያ ልዩ ዞን፣ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፣ሰሜን ሸዋ፣አዊ ዞን፤ከአፋር ክልል ዞን 3 እና 5፤ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል አሶሳ፣መተከል፣ከማሺ እና የማኦ ኮሞ ልዩ ዞን፤ከጋምቤላ ክልል አኙዋክ፣ማዣንግ፣ንዌር እና የኢታንግ ልዩ ዞን፤ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ስልጤ፣ሀዲያ፣ከምባታ ጠምባሮ፣ዳዉሮ፣ወላይታ፣ጎፋ፣ሁሉም የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ድሬዳዋ፣ ሐረሪ

እና በአዲስ አበባ፣ ላይ ከ60-535 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ1-28 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ::


ባለፈው የሴፕቴምበር ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከአማራ ክልል ሰሜን፣ማዕከላዊና፣ምዕራብ እና ደቡብ ጎንደር፣ ደቡብ ወሎ፣የኦሮሚያ ልዩ ዞን፣አዊ ዞን፣ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፤ ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ቄለም ወለጋ፣ቡኖ በደሌ፣ኢሉባቦር፣ሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፣ምዕራብ እና ደቡብ ምዕራብ ሸዋ፣ቦረና፣ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፣ጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ፣አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፤ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል አሶሳ፣ከማሺ እና የማኦ ኮሞ ልዩ ዞን፤ ከጋምቤላ ክልል ኑዌር፣አኙአክ፣ማዣንግ እና የኢታንግ ልዩ ዞኖች፣ሁሉም የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፤የደቡብ፤የማዕከላዊ እና የሲዳማ ክልል ዞኖች እንዲሁም ሀረሪ፣ድሬዳዋ እና በአዲስ አበባ ላይ መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ የዝናብ መጠን የተመዘገበ ሲሆን፣የአፋር፣የትግራይ፣የምስራቅ እና ምዕራብ አማራ ዞኖች ላይ ከመደበኛ በታች የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3) ።

በሌላ በኩል የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በምስራቅ፣በሰሜን ምስራቅ እና በደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በአብዛኛዎቹ ቀናት ላይ ከ40 ዲ.ሴ በላይ ሆኖ ተመዝግቧል (ምስል 1) ።


ከ40 ዲ.ሴ በላይ የተመዘገበባቸውን ሥፍራዎች ለመጥቀስም ያህል :-





**ምስል 1 የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ**




ካርታ 1 ኢ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2023 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ





ካርታ 2 ኢ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2023 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2023 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር

# እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2023 የነበረው የአየር ጠባይ በእርሻ ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ


ባሳለፍነው የሴፕቴምበር ወር ለክረምት ዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታ የሚፈጥሩ የአየር ሁኔታ ክስተቶች የነበሩ በመሆኑ በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ከቦታ ቦታ በመጠን ይለያይ እንጂ በስርጭት ረገድ ብዙ ቦታዎችን ያደረሰ የእርጥበት ሁኔታ ነበራቸዉ፡፡ የተተነተኑ ወርኃዊ የአፈር ውስጥ እርጥበት ጠቋሚ መለኪያ (Moisture Index) እንደሚያመለክተው በተለይም በምዕራብ አጋማሽ፣ በመካከለኛዉ፣ በምስራቅና በደቡብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ብዙ ቦታዎችን የሸፈነ እርጥበት ነበራቸው፡፡ ይህም ሁኔታ የአፈር ውስጥ እርጥበትን ከማሻሻል ጋር ተያይዞ እድገታቸውን ላልጨረሱና በተለያየ እድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የመኸር ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች የሚያስፈልጋቸውን ውሃ ከማገኘት አንጻር ገንቢ ሚና ነበረው፡፡ በተጨማሪ በአርብቶ አደርና በከፊል የአርብቶ አደር አካባቢዎች የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት አዎንታዊ አስተዋፅዖ ከማበርከቱም በላይ ሰው ሰራሽም ሆነ የተፈጥሮ ምንጮችን ከማጎልበት አንፃር አዎንታዊ ሚና ነበረው፡፡ እንዲሁም ቀስ በቀስ በተለይም የሁለተኛው እና የመጨረሻዎቹ አስር ቀናት ላይ ወደ ደቡብ የተስፋፋዉ እርጥበት በደጋማው አካባቢ የማሳ ዝግጅት ለማከናወንና የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውኃ አቅርቦትን ከማሻሻል አንጻር በጎ ሚና ነበረው፡፡ በተጨማሪም ተከታታይነት የነበረው እርጥበትና በመደበኛ ባህሪያቸው በእርጥበት መብዛት በሚታወቁና የመሬት አቀማመጣቸው ተዳፋትና ውሀ ገብ በሆኑ አካባቢዎች ላይ የነበረው የእርጥበት መብዛት በሰብል ማሳዎች ላይ የውሃ መተኛት ያስከተለ ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ እየተከናወነ በሚገኘዉ የእርሻ ስራ እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ጎን ነበረው፡፡ እንዲሁም የነበረው ከፍተኛ እርጥበት ለአረም መስፋፋትም ለሰብል በሽታዎች መከሰት ምቹ ሁኔታን የፈጠረ ነበር (ካርታ




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2023 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉው የሴፕቴምበር ወር በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ ዋና ዋና ተፋሰሶች ላይ የእርጥበት ሁኔታው በመጠንም ሆነ በስርጭት እየተሻሻለ እና እየጨመረ እንደነበር የተተነተኑ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ በዚህም መሰረት በአብዛኛው አባይ፣ ኦሞጊቤ፣ ባሮ አኮቦ፣ የላይኛውና የመካከለኛው ስምጥ ሸለቆ፣ የላይኛውና የመካከለኛው አዋሽ፣ በጥቂት ደቡባዊ ተከዜ፣ በጥቂት የላይኛው ዋቢ ሸበሌ እና ገናሌዳዋ አዋሳኝ ተፋሰሶች ላይ ከእርጥበታማ እስከ ከፍተኛ የእርጥበት ሁኔታ ተስተውሎባቸው ቆይተዋል፡፡ በተጨማሪም የመካከለኛው ገናሌ ዳዋ፣ ዋቢ ሸበሌ የመካከለኛው አባይና ተከዜ፣ ጥቂት የታችኛው አዋሽ ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ የእርጥበት ሁኔታ የተስተዋለባቸው ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት አካባቢዎች ላይ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ የገጸ ምድርና የከርሰ ምድር ውኃን ከማሻሻል እንዲሁም የወንዞች እና የምንጭ ውኃን ከማጎልበት አንጻር አዎንታዊ ሚና እንደነበረው ተስተውሏል፡፡ በሌላ በኩል በአዋሽ እና በአባይ ተፋሰሶች ላይ የተስተዋለው ከፍተኛ የሆነ የእርጥበት ሁኔታ በተፋሰሶቹ በሚገኙ በቆቃ እና ፊንጫ ግድቦች ላይ ጫና ፈጥሮ እንደነበር የተተነተኑ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ የተቀሩት ተፋሰሶች ግን ደረቅና ከፊል ደረቅ የአየር ሁኔታ ስር ቆይተዋል፡፡





ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

# እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2023 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ የክረምት ድንበር ወደ ደቡብ አቅጣጫ ከሚያደርገው እንቅስቃሴ ጋር ተያይዞ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በደቡብ የሀገሪቱ አጋማሽ ላይ እየተጠናከሩ ይሄዳሉ፡፡ ስለሆነም የደቡብ እና የደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ በተጠናከረ ሁኔታ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸውን የሚያገኙ ሲሆን፣ በተመሳሳይ ሁኔታም በምዕራብ እና በደቡብ ምዕራብ ዝናቡ ቀጣይነት ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም የሰሜን አጋማሽ የኢትዮጵያ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማ እና ነፋሻማ የአየር ጠባይ ጎልቶ ከመታየቱ አንጻር የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ መጨመር ያሳያል፡፡

በሚቀጥለው ወር ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ ገጽታ እንደሚኖራቸውና በሂደትም ወደ ደቡብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ ያገኛሉ፡፡ በተጨማሪም በጸሀይ ሀይል በመታገዝ ከሚጠናከሩ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በመነሳት በምዕራብና በደቡብ አጋማሽ አከባቢዎች ላይ ከባድ መጠን ዝናብ እንደሚኖር አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡

በአጠቃላይ በመጪው ወር ከኦሮሚያ ክልል ምዕራብ፣ ምሥራቅ እና ቄለም ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ጅማ፣ ቡኖ በደሌ፣ አርሲና ባሌ፣ ምዕራብና ምሥራቅ ሐረርጌ፣ የቦረና፣ የጉጂና የምዕራብ ጉጂ ዞኖች፣ ድሬዳዋና ሐረሪ፤ የጋምቤላ ክልል ዞኖች፤ የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ዞኖች፤ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ የምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የሃዲያ፣ ሃላባ፣ የከምባታና ጥንባሮ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የምዕራብ፣ የመካከለኛዉና የደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ ምዕራብና ምስራቅ ጎጃም፣ እንዲሁም የባህር ዳር ዙሪያ እና አገው አዊ፤ እንዲሁም ከሶማሌ ክልል ከሲቲ ዞን በስተቀር ሁሉም ዞኖች በአብዛኛው ከመደበኛ ጋር የተቀራረበ እና በጥቂት ሥፍራዎች ደግሞ ከመደበኛው በላይ ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል፡፡በተጨማሪም አልፎ አልፎ ከሚፈጠሩ ጠንካራ ደመናዎች በሰሜንና በደቡብ ወሎ፤ የደቡብ፣ የደቡብ ምስራቅ እና የምስራቅ ትግራይ ክልል ዞኖች፤ እንዲሁም በደቡብ አፋር ዞን 3፣ 4 እና 5፤ ምዕራብ አርሲ አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከኦክቶበር 1-31/2023 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2023 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥለው የኦክቶበር ወር ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ ገጽታ እንደሚኖራቸውና በሂደትም ወደ ደቡብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ እርጥበት እንደሚኖር ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም ወቅታዊ ዝናብ ማግኘት በሚጀምሩትና ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው ለሆኑት የደቡባዊው የሀገሪቱ ክፍሎች በደጋማ አካባቢዎች ቀደም ብሎ የማሳ ዝግጅት ለማድረግና ዘር ለመዝራት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ በተጨማሪም ወደ ደቡብና ደቡብ ምስራቅ የሚያደርገው መስፋፋት በስፋት በአካባቢው ለሚኖሩት አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለግጦሽ ሣርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት ጥሩ አስተዋጽዕ እንደሚኖረው ይጠበቃል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታም በምዕራብ እና በደቡብ ምዕራብ ዝናቡ ቀጣይነት የሚኖረው በመሆኑ ቀደም ብለው ለተዘሩና አልፎ አልፎ ፍሬ በመሙላት ላይ ለሚገኙ፣ በተለያየ ምክንያት ዘግይተው ለተዘሩና በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ለመኸር ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም በአካባቢው ለሚገኙ አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለመጠጥ ውሃ አቅርቦትና ለግጦሽ ሣር ልምላሜ የጎላ አስተዋፅኦ ይኖረዋል። በሌላም በኩል በጸሀይ ሀይል በመታገዝ ከሚፈጠር ከባድ ዳመና ጋር ተያይዞ በምዕራብ እና በደቡብ አጋማሽ በተለያየ ቦታዎች ላይ የሚጠበቀው ከባድ ዝናብ በተዳፋትና ለጎርፍ ተጋላጭ

በሆኑ አካባቢዎች ላይ የአፈር መሸርሸርና እንዲሁም በእርሻ ማሳዎች ላይ የውሃ መተኛት ሊያጋጥም ስለሚችል አርሶ አደሮችና የሚመለከታቸው አካላት ከወዲሁ በግብርና ባለሙያዎች በመደገፍ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚኖርባቸውና የተለያየ ዘዴን ተጠቅመው ውሃን ለሚያቅቡ አካባቢዎች ግን የሚጠበቀው ዝናብ ጥሩ አጋጣሚ ስለሚሆን አጋጣሚውን በአግባቡ መጠቀም ያስፈልጋል። በተጨማሪም ሰብሎች ቀድመው በሚደርሱባቸው መኸር አብቃይ በሆኑ ቆላማ አካባቢዎች የሚጠበቀው እርጥበት ጉዳት እንዳያደርስ በየጣልቃው የሚኖረውን ደረቅ ቀናቶች በመጠቀም የደረሱ ሰብሎችን በወቅቱ በማንሳት አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2023 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በውሀው ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥለት የኦክቶበር ወር በአብዛኛው በምዕራብ አጋማሽና ደቡብ ምዕራብ በሚገኙ የሀገሪቱ ዋና ዋና ተፋሰሶች ላይ የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ እንደሚኖር የትንበያ መረጃዎች የሚያመላክቱ ሲሆን፣ በሂደትም በጋ የዝናብ ወቅታቸው ወደ ሆኑት የደቡብና ደቡብ ምስራቅ በሚገኙ የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ የእርጥበት ሁኔታው እንደሚጠናከር ይጠበቃል፡፡ በዚህም መሰረት በአብዛኛው የላይኛውና የመካከለኛው አባይ፣ የኦሞጊቤ፣ የሥምጥ ሸለቆ፣ የገናሌዳዋ፣ የዋቢ ሸበሌና የኦጋዳን እንዲሁም የባሮ አኮቦ ተፋሰሶች ላይ ከእርጥበታማ እስከ ከፍተኛ የእርጥበት መጠን እንደሚያገኙ ይጠበቃል። በተጨማሪም የመካከለኛው አዋሽ፣ የደቡባዊ ተከዜ ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ እርጥበት ሊኖር እንደሚችል የሚጠበቅ ሲሆን፣ የሚኖረው እርጥበትም በተለይም በጋ የዝናብ ወቅታቸው ለሆኑት የደቡብና ደቡብ ምስራቅ ለሚገኙት ተፋሰሶች ላይ ለውሃ ሀብት ግብዓት ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡